# ታሪክ እንዳይረሳ፡ የእፀገነት ሰብሉ ገድል

ዕፀገነት በወጣትነቷ የሀገርና የወገን ፍቅር ተሰምቷትና አንገብግቧት ገና በተማሪነት



ዘመኗ በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ በመሳተፍ ፊላጭ ቆራጩን የአፄ ሥርዐት በጽናት ታግላለች፡፡ ከንግድ ሥራ ኮሌጅ ተመርቃ በብሔራዊ ትምባሆ ሞኖፖልና በሼል ኩባንያ ሠራተኛ በነበረችባቸው ወቅቶች በሠራተኛ ማህበር ጉልህ አስተዋጽኦ አድርጋለች፡፡ ዕፀገነት የኢሕአፓ አባል ሆና ፋሽስታዊውን የወታደሮች መንግስት ስትታገል በአውሬዎቹ እጅ ወድቃ ከሰው ልጅ አቅም በላይ የሆነ ስየል ተፈጽሞባታል፡፡ ገላዋን ተተልትላ፣ የእጅና የእግር ጥፍሮቿ በጉጠት ተነቅለው፣ ዕፀገነት ሁሌም ሁሌም ስቃይዋን በሁድዋ ውጣ፣ ፊትዋን በፈገግታ ትሞላው ነበር፡፡ ሊገድሏት ከእስር ቤት ሲያወጧት ወደ እስረኛው ዞር ብላ "ሞት ለፋሽሽቶች! ድል ለኢሕአፓ!" በማለት ደጋግማ ጮኻ፣ እየተገፈተረችና እየተዳፋች ወጣች፡፡ መጋቢት 13 ቀን 1970 ዓ.ም. በጥይት ደብድበው ገድለዋት፣ አስከሬኗን ቀድሞ በምትሠራበት በትምባሆ ሞኖፖል በራፍ ላይ ጣሉት፡፡ በዚያን እለት ከሰማንያ በላይ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች በጥይት ተደብድበው ተገድለዋል፡፡ ከነዚህ መሀል፡-

1. ሩቂያ ሓመድ 2. ጌታቸው አሰፋ 3. ክፍሌ ተሰፋ ገ/ኤል 4.ግርማ ደምሴ 5. ሰላትየል ኃ/ሥላሴ 6. አስፋው ተድላ 7. ፍቃዱ ወ/ጊዮርጊስ 8. ትዕግስት ዮሐንስ 9. ናደው ደምሴ 10. ቦጋለ ደምሴ 11. ግርማ ማጋጋቲ 12. በቀለ ቶሎሳ 13. ፍሬህይወት ደመቀ 14. ሃረገወይን ደመቀ (የ14 አመት ታዳጊ ወጣት የነበረች) 15. ተቋመ ደመቀ 16. ጀርጊ ዲናገ ይጠቀሳሉ። ታሪክ እንዳይረሳ፣ ግቡንም እንዳይስት ዛሬም ድረስ የነኛ ታጋዮች ደም ይጮኻል!